# የገናን በዓል በኢህአዴግ ኑዛዜያዊ ቃል እንዝናና

[በወንድወሰን ተክሉ-ጋዜጠኛ]

 * እንካን ለገና በዓል በሰላም አደረሳችሁ-

ሰላም ጤና ይስጥልኝ እንደምን ሰነበታችሁ ውድ አንባቢዎቼ?

የክርስትና እምነት ተከታይ ለሆናችሁ ሁሉ የእንኳን ለዛሬዋ የጌታችን እና መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደተ በዓል በሰላም አደረሳችሁ የሚለውን መልካም ምኞቴን በቅድሚያ ሳስተላልፍላችሁ በጥልቅ ኢትዮጵያዊ እውነተኛ ፍቅር  ነው።

የዓለም መድሃኒት የሆነው አዳኙ [መሲሁ]ኢየሱስ ባይወለድ ኖሮ የምድሩ ገዢዎቻችን የሚያስቀዩን ስቃይ አንሶ የሰማዩም ይቀጥልብን ነበርና [ዛሬም መጽደቅና መኮነን ቢኖርም ማለቴ ነው] እለተ ውልደቱን እንኳን ተወልድክልን በማለት እነሆ እኛ በአባታችን አዳም ዘላለማዊ ሞት ተፈርዶብን የነበርን ሰዎች ነጻ ስላወጣህን ልደትህን በየዓመቱ በመዘከር በፌሽታ፣በደስታ፣በቀለጠ ድግስ[ያለው ነው እሚደግሰው የሚል ድምጽ ይሰማኛል] እና ወይም በቁዘማ፣በቁጭት፣በተመልካችነትና በሀዘንም ሆነን እያከበረን ዘንድሮን ደርሰናል።

የዓለም መድሃኒት መድሓኒያለምም እንኳን ተወለደ!!ለሁላችሁም መልካም የገና በዓል በያላችሁበት ይሁንላችሁ!!

**እንደ ኢየሱስ ነጻ የሚያወጣን ነጻ አውጪ ማየት ናፍቆኛል-

ለአርእስቱ ንሰሃ ገብቻለሁና አትስጉ ጌታን መሳይ ሰው የለምና እንዴት እሱን መሳይ ነጻ አውጪ የእኛ ብጤ ሰው ናፈቀኝ ይባላል በሚል መንፈስ ለአባባሌ አትስጉ። የጨነቀው እርጉዝ ያገባል ይባል የለ? እናም እኔም [እኔ ስል እኛ ኢትዮጵያዊያን ማለቴ ነው] በጭንቅ ያለሁ፣ጭንቅ ጥብብ ብሎኝ ጌታን መሳይ ነጻ አውጪ [ከ2010ዓመት በፊት በፍልስጥኤማ ቤተልሄም ጌታ ሲወለድ የአይሁድ ሕዝብ በሮማው ቄሳር አረመኔ ሰራዊት ተወረው በቅኝ ግዛት የሚሰቃዩ ህዝቦች ነበሩ] ብናፍቅ ምን የሚያስኮንን ምኞት ተመኘሁ? ጭቆና ቀለም የለውም ጨቃኙ ቢለያይ እንጂ።

እናም ጨንቆኝ ጭንቅ ቢለኝ የምታቅፈውን ያጣች የተጠየፈችውንና የናቀችውን ለማቀፍ "የዛሬስ ብርድ ቆማጣ ያሳቅፋል" ተረትን ተርታ አቅፋ እንዳደረችዋ እንስት አትቁጠሩብኝና በእርግጥ ለግል ስልጣኑና ጥቅሙ ሳይሆን መጀመሪያ ለ12ቱ የይሁዳ ነገድ ልጆች ለሆኑት አይሁዳዊያን ቀጥሎ ደግሞ ለመላ የሰው ልጅ ደህንነትና እኛን ለማዳን ሲል እራሱን በቀራኒዩ ለሰቀለው [ለተሰቀለው አላልኩም-ባለው ስልጣንና ሃይል በመጠቀም የሰቀሉትን የሮማ ወታደሮችን ጫፉን እንዳይነኩት ማድረግ እየቻለ እንዲሰቅሉት በመፍቀዱና በመተባበሩ ለማዳን ሲል እራሱ የሰቀለ ስል ነው እምገልጸው]ነጻ አውጪው ጌታን መሳይ ኢትዮጵያዊያን ለሀገርና ለህዝብ በጋራ የሚነሳን መሪ እጅግ የናፈቁበት ወቅት ቢኖር አሁን ያለንበት ወቅት አይደለምን?

በነገራችን ላይ እኛ እኮ ከጌታ ምህረት ተቋዳሽ የሆንነው በልበ ድንጋዮቹ አይሁዳዊያን ጥመትና እምቢታ ምክንያት ነው በማለት አይሁዳዊያኑ ጌታን ቢቀበሉት ኖሮ እኛ ምን ይውጠን ነበር ለምትሉ ተጠራጣሪ የቶማስ ዘሮች መልሴ የማያልቅበትና የማይሳነው ፈጣሪ አምላክ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ በሌላ ሁለተኛ ድንግል ሴት ሁለተኛ ልጅ [ያው የመጀመሪያው ኢየሱስ ተወልዶ የለ] ሆኖ ተወልዶ ያድነን ነበር ወይም በቃ "የአብርሃምና የያእቆብ ልጆች 12ቱ የይሁዳ ነገደ የተቀበለው ዓለም ተቀበለው"በሚል ማሳረጊያ ውሳኔው የአዳኝነቱን መድህን ተጠቃሚ ያደርገናል እንጂ እንደኛዎቹ ገዢዎች ከደጁ ሜዳ ላይ በትኖን በሩን ይዘጋብናል ብዬ እንዳልምን ለእኛ ያለው ፍቅር ያግደኛል።

ኢትዮጵያዊያን ለግል ስልጣንና ለራስ ዝና ሳይሆን ለሀገርና ለወገን ህልምና ዓላማ ያለው መሪ ለማግኘት እጅግ እንደተራቡ ነው። ከርሃቡ መጥናት የተነሳም በጤኔ ይሙቱ ይሆን እያልኩ የሰጋሁበትም ወቅት በርካታ ግዜ ነው።

ሀገራዊ ህልምና ራእይ ያለውን ነጻ አውጪ መሪና ድርጅት ተርበው ተርበው ጤኔው ሊመታቸው ሲል እራሳቸው ብድግ ብለው እርሰበርስ እየተመራሩ ካገታቸው ጨቃኙን የባቢሎን ግንብ ለማፈረራስ መደርመሻ ያለው በመደርመሻ፣አካፋና ዶማ ያለው በአካፋና ዶማ ምንም የሌለው በጥፍሩ እየባጠጠ የጠጠረውን ግንብ አለት ሲታገሉ ማፈራረስ መቻላቸውን እየጮሁ ተመለከቱ።

የህወሃት መራሹ ስርዓት ጨቋኝ ህግጋቶችና ጭካኔ የተሞላበት አገዛዝ የሃሙራቢ ሀገር የሆነችውና ዛሬ በነዳጅ የብታ የአሜሪካንን ለሃጭ አዝረብርባ በመሳብ ልትወረር የቻለችዋ ኢራቋ የባቢሎን ግንብ አቻ ከፋፋይና የጠነከረ አለት ሆኖ እያስጨነቀ ያለ ሲሆን የባቢሎን ግንብ በባቢሎናዊያን እንደፈረሰ ሁሉ ኢትዮጵያዊያንም የነገሰባቸውን ግንብ ለማፈራረስ በያለበት ግን በህብረት መናድ ጀምረዋል።

በዚህ የህወሃት መራሹን የባቢሎን ስርዓት ለማፈራረስ እየተካሄደ ባለው ህዝባዊ እርብርብና ግብግብ ሁኔታ ስሙ ጎልቶ እየተሰማና በቁመቱም ከሁሉ በልጦ እሩቅ ባሉ ወገኖችም ዘንድ መታየት የቻለ አንድሰው ጉዳይን አርእስት አድርጌ ለመጻፍ እየተዘጋጀሁ ሳለ ነው ድንገት ይህንን የምታነቡትን ይዘት ያለው መጣጥፍ ለገና በዓል ይሆን ዘንድ ልጽፍ የቻልኩት።

"የአቶ ለማ መገርሳ ተመኩሮ" በሚል አርእስት ስር ላዘጋጅ ያሰብኩትን ሀተታ ለማክሰኞ ይቆየኝ ብዬ የዛሬውን "የገናን በዓል በኢህዴግ ኑዛዜ መዝናንት" በሚል ርእስ እንዳቀርብ ያደረገኝ የምናከብረው የገና በዓል ሲሆን በተደራቢነት ግን በአራቱ የኢህአዴግ ፓርቲ አመራሮች የተሰጠው መግለጫም በአናዳጅነቱና በአስገራሚነቱ ብቻ ሳይሆን በአዝናኝ አስቂነቱም ስላየሁት አንባቢዎቼም እለቱን በአዝናኝ ሁኔታ እንዲያሳልፉ ከመሻት ነው።

**የከሸፈው ኢህአዴግ አዝናኙ ኑዛዜ-

ተመሳስለው ያልተመሳሰሉ አራት መሪዎች በአንድ ስፍራ ሆነው ስለሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ላይ ተመርኩዘው ስለ ድርጅቱ ያላቸውን እይታና መረዳት ሲገልጹ ሰምተናል።

አራቱ አመራሮች አንድ ለሶስት በሆነ አሰላለፍ የሀገራችንን ችግርና የአፈታት ሁኔታን ሲያብራሩ ሶስቱ የተለመደውን ፕሮፖጋንዳ [ሪቶሪክ] ድግግሞሽን መላልሰው ሲያስተጋቡ ከመካከላቸው አንደኛው በእርግጥም ያለንበትን ችግርና ምንጬን በትክክለኛ ሁኔታ ሲያስረዳም ማስተዋል ችለናል።

የመፍትሄዎች ሁሉ መነሻ የችግሩን መፈጠርና የችግሩን መንስኤ አምኖ በመቀበል ነው። የችግሩን ምንጭ አወላግዶ የሚያይና ያገጠጠና ያፈጠጠን ችግር በሽንጋይ የቃላት ጋጋታ በፕሮፖጋንዳ ለመግለጽ መጣር የተፈጠረውን ውስብስብ ቀውስና ችግርን አወሳስቦ መልስ አልባ ከማድረግ ውጪ የሚያመጣው ፋይዳ የለም።

ሆኖም ሶስቱ አመራሮች እራሳቸውንና ድርጅታቸውን ለመታደግ በሚያደርጉት መውተርተራዊ ድርቅና ውስጥም አንድ ጎልቶ የተስተዋለው እውነታ ጸረ ሰላም ሃይሎች የሚለው መዝሙር በስርዓቱን ለማፍረስ በሚፈልጉ ሃይሎች አባባልና መሰል የሆኑ አጠቃቀሞችን ያስተዋልንበትም ነው- ኑዛዜያዊ በመሰለ ሁኔታም ሁሉንም በራሳቸው ድርጅት ላይ የደፈደፉበትን ክስተት ሆኖም ታይታል ማለት ይቻላል የሶስት ለአንድ የተከፈሉት መሪዎች አነጋገር።

እጅግ ያሳዘኑኝ አራት ሰዎች መግለጫ። ኖኖኖ. ይቅርታ መግለጽ የምፈልገው -እጅግ ያሳዘኑኝ ከአራቱ ሰዎች ያሳዘኑኝ የሶስቱን ሰዎች መግለጫ በሚል ሲሆን አመላለሳቸው ከወትሮው ሁኔታዬ በተለየ መልኩ እየተዝናናሁ እና እየሳቅኩ [ማሽላ ሲያር ይስቃል እንዳትሉና] ያደመጥኩት በመሆኑ አግራሞት ጭሮብኛል።

1ኛ-አዲስ የተገኘውን ጭራቅ እስቲ ይተዋወቁ- ስሙም ጥገኝነት ይባላል

በመጀመሪያ ደረጃ እንድሜና ምስጋና ጭራቁን ጥገኛ ላገኘው ህወሃት ይሁንና ሁላችሁም ነጻ ወጥታችሃል።

በተለይም ነፍጠኛ ትምክህተኛ፣ጠባብ፣አሸባሪ፣የግንቦት ሰባት ሴረኛ፣የግብጽና ሻእቢያ ተባባሪ እየተባላችሁ ለዓመታት ሳይሆን ለዘመናት የተብጠለጠላችሁ ሁሉ ህወሃትን አመስግኑና ዛሬ የኢህአዴግ ሃያል ጠላት የሆነው ጥገኝነት ተገኝታልና ደስ ይበላችሁ- ስማችሁ በጻድቃኖቹ ህወሃት አልተጠራምና።

የ18ቀኑ ዝግ ስብሰባ ለካንስ ይህንን ጭራቅ ፍለጋ ኑራል በር አዘግቶዋቸው ሲያነታርካቸው የቆየው?

የሚገርም ግኝት ነው። ይህ ጭራቁ ጥገኝነት ተጠያቂ የሆነበትን ጥፋትና ተግባራቶችንስ አውቃችሃል?

አመራራዊም በሉት ድርጅታዊ ግምገም[ቆረና ይላሉ የእነ አቦ ለማ ልጆች]እንግዳ ባልሆነበት ኢህአዴግ የግምገማ ታሪክ ውስጥ በየዓስር ዓመቱ እንደዘንድሮው ለችግሮችና ለድርጅታዊ መፈራረስ ትልቁን ስራ እየሰራ ያለን አዳዲስ ጭራቆችን ሰይሞ መውጣት ልምድ ሆናል።

ቦናፓርቲዝም-በአንድ ወቅት[በ1993ዓ.ም] የሚል ጸረ ህወሃት/ኢህአዴግ ጭራቅ ጠላት በህወሃት ማህጸን ውስጥ ተወልዶ ማደጉን አፈር የለበሱት አቶ መለስ ሲነግሩን ያንን ቦናፓርቲዝም የተባለን ጭራቅ ዓይነቱን ለማወቅ አዳሜ መዝገበ ቃላትን እያተራመሰ ያገላብጥ ጀመር።

ቦናፓርቲዝም በመዝገበ ቃላት ውስጦ ውልፍት አልል ሲል ወደ እንግሊዘኛው እየዘለሉ የተረሱ የማርክስ፣ሌኒንና ኤንግልስ መጽሃፍቶች ሌት ተቀን ይኮመኮሙም ጀመር።

** በዘንድሮ ግምገማ የተገኘው ጠላት ጭራቁ ጥገኛ ተጠያቂ የሆነባቸውን ጥፋቶች እስቲ እንይ-

**1ኛ-በምስራቅ ኢትዮጵያ ለተፈጠረው የጎሳ ግጭት -ተጠያቂው ጥገኛው

**2ኛ-በሀገሪቷ ውስጥ የትግራይና ህወሃት የበላይነት አለ ለማለት ያስቻለው- ተጠያቂው ጥገኛው

**3ኛ-ለከትየለሽ የሙስና ዘረፋ-ተጠያቂው ጥገኛው

**4ኛ-ለአመራሩ ሃላፊነቱን መወጣት እንዳይችል አድርጎ ለሀገሪቷ በቀውስና አደጋ ላይ መድረስ -ተጠያቂው ጥገኛው

**5ኛ-ለመልካም አስተዳደር መጥፋትና ለኪራይ ሰብሰባነት መንገስ -ተጠያቂው ጭራቁ ጥገኛው

**6ኛ-የፌዴራሊዝሙ ስርዓት በሀገሪቱ ውስጥ ለተፈጠረው ግጭት፣ፓለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊ እና የጸጥታ ችግር - ተጠያቂው ጭራቁ ጥገኛ እንደሆነ በአንድ ቦታ ከተኮለኮሉት አሳዛኝ ሶስት ጫሂዎች አንደበት ተደጋግሞ ተነገረን።

ጎበዝ እንግዲህ ይህን ጥገኛ ጭራቅ የገባበት ገብተን በመያዝ [እስካሁን አልተያዛም] ሀገራችንን መታደግ ይኖርብናል። እናም ጭራቁን ጥገኛ ለመያዝ የሚኖርበትን ቦታ ማወቅ ይገባናልና ለመሆኑ ይህ ጭራቅ ጥገኛ ጠላታችን የት ነው የመሸገው ? ምንስ ይመስላል? የትስ  ነው የሚገኘው? ብለን በመጠየቅ ነው እንግዲህ የምንጀምረው።

ጭራቁን ጥገኛ ዶክትሬት ያላጠና የሚያየውና የሚያገኘውም ዓይደለም።
ግን ዶ/ር ደብረጺዮን ባይኖሩ ኖሮ ይህ አረመኔ የሆነውና የሀገርና የህዝብ ጠላት የሆነው ጭራቁ ጥገኛ ባልተገኘና ዝንተዓለም ባሰቃየን ነበር።

ድንቁ ዶክተር ክቡር ደብረጺዮን ይህ ጭራቁ ጥገኛ በትግራይ ክልል ህወሃት በተባለ ድርጅታቸው ውስጥ ተወልዶ ያደገና የፈረጠመ መሆኑን በመግለጽ እሱን ለመዋጋት የእኛን የኢትዮጵያዊያንን ትብብርና ድጋፍ በተማጽኖ በመለመን ጭምር ገልጸውልናል።

ጭራቁን ጥገኝ በትግራይ ውስጥ ብቻ ተዋግተን ማሸነፍ የሚቻለን ስላልሆነ በአማራ፣በኦሮሚያ ክልልና በሀገር ደረጃ በመላ ኢትዮጵያ ይህንን ጥገኛ መዋጋት አለብን ሲሉ ተማጽነዋል።

እኔን በጣም አዝናንቶኛል አጠቃላይ የሶስቱ ሰዎች ኑዛዜና የአንደኛው ስውዬ ቁርጥ ሁኔታ ደግሞ አስደምሞ ተስፋም አስጭሮኛል።

የተከሰቱ ማንኛውንም ድርጅታዊ፣ህዝባዊና ሀገራዊ ችግሮችን ወደ የትምክህተኞ፣ጠባቦች፣የግብጽና ሻእቢያ ተላላኪዎች፣ወደ አሸባሪዎች መንደር በማሽቀንጠር በህዝብ ጥያቄ ላይ በመሳለቅ የሚታወቀው ኢህአዴግ በታሪኩ ለመጀመሪያ ግዜ የችግሮቹ ምንጭና ጥፋተኛው ሁሉ እራሱ ድርጅቱ መሆኑን በኑዛዜ መልክ የተናዘዘበት ወቅት ቢኖር ዘንድሮ ያውም ይህ ባለፉት ሳምንታት ውስጥ ለ18ቀናት የተካሄደው ስብሰባ እንደሆነ መግለጽ ይቻላል።

እስቲ በዚህ መልክ ላስቀምጠው - በሀገሪቷ ውስጥ ለተፈጠሩት ዘርፈ ብዙ ችግሮችና ግጭቶች በሙሉ ተጠያቂውና ሃላፊው የስራ አስፈጻሚው አመራር አካል ሲሆን ለዚህ አካል ጥፋተኝነት  መንስኤው ደግሞ የብቃት ማነስና የስርዓቱ ጉድለት ሳይሆን በትግራይ ህወሃት ውስጥ አሽምቆ ያለው ጭራቁ ጥገኛ የተባለ ሃይል ነው በማለት ተደምድሟል።

እንግዲህ የዚህ ሁሉ ጥፋትና ውድመት ተጠያቂ የተደረገውና ስልጣንን በእርስትነት ለእኔ ብቻ ይገባኛል በማለት እራሱን የሀገሪቷ ብቸኛ የበኩር ልጅ በማድረግና ሌሎችን ሁለተኛና ሶስተኛ ዜጋ በማድረግ ተግባሩ የተገለጸው እጅግ አደገኛው ጭራቁ ጥገኛ የተወለደው ትግራይ፣ያደገው በህወሃት የሚጠራውና የሚኖረው በህወሃት ውስጥ ሆኖ ሳለ እራሱ ህወሃት በሊቀመንበሩ ዶ/ር ደብረጺዮን እየተነገረን ሳለ እንዴት አድርገን ነው ከአዲስ አበባ፣ከኦሮሚያ፣ከአማራና ሌሎች ክልሎች ሄደን እምንታገለው?

ችግሩን አወቁ ግን ችግሩን እንዴት እንደሚያቆሙ አለማወቅ ብቻ ሳይሆን አለመቻልን አየንባቸው የሚለው ድምዳሜያዊ እይታ ይህን የአይጦች ተረት አስታወሰኝ።

በአደገኛ ድመት የተቸገሩ አይጦች ታሪክ። በድመቲቱ ጨፍጫፊነትና እጅግ የህልውና አደጋነት ላይ ተሰብሳቢ አይጥ ሁላ ጭራዋን እያወጣች ተናግራ ከተስማማች በሃላ እንዴት እናቁመው በሚለው ሀሳብ ላይም በጠላታቸው ድመት አንገት ላይ ቃጭል አስሮ የቃጭሉን ድምጽ በመስማት ከመበላት እንደሚድኑ የተስማሙበትን ታሪክ ነው ያስታወሰኝ።

ድመቲቱ አንገት ላይ የደውል ቃጭል ማሰር የድመቲቱን እንቅስቃሴ ጠቃሚ ዲቫይስ በመሆኑ መፍትሄነት ተስማምተውና አጨብጭበው ማን ድመቲቱ አንገት ላይ ያንን ቃጭል ይሰር የሚለውን የሽማግሌውን አይጥ ጥያቄ ግን መመለስ የሚቻሉ ባለመሆናቸው ምክንያት ስብሰባቸው ያለውጤት ተበትኖ በድመቲቱ የመበላት እጣፈንታቸው እንደቀጠለ ሁሉ ዛሬም የህወሃቱ መሪ አደገኛ ያሉትን የጥገኛ ሃይል መኖሩን ገለጹ እንጂ ሊወስዱ ስለሚችሉት እርምጃ አልገለጹምም የሚቻላቸውም አይደለምና ሁኔታው ሲቀጥል ይታያል።

**2ኛ- ባለጉዳዮችና መብታችሁ እንዲከበር የምትፈልጉ ሁሉ ጉዳያችሁንና መብታችሁን ለማስፈጸምና ለማስከበር ጉልበትና ሃይል እንድትጠቀሙ ጠ/ሚ ሃይለማሪያም ፈቅደዋል-

በመልካም አስተዳደር እጦት እየተንገላታህ ያለህው  ውድ የሀገሬ ህዝብ ሆይ እነሆ ከዛሬ ቀን ጀምሮ የትኛውንም ጉዳይህን ለማስፈጸም ችግር ካጋጠመህ በራስህ ጉልበትና ሃይል በመጠቀም እያመላለሰም ሆነ አይቻልም እያለህ ያስቸገረህን ባለስልጣን አስገድደህ ማስፈጸም እንደምትችል የተከበሩትና የህዝብን ችግር የተረዱት ክብር ጠ/ሚ/ር አቶ ሃይለማሪያም ደሳለኝ ፍቃድ ሰጥተውሃል።

ይህንን ለማስፈጸም ደግሞ አቅም የለኝም የምትል ከሆነ በግሩፕና በቡድን ከተደራጀህ በየቢሮው እየገባህ እምቢ  ያልህን ባለስልጣንም ሆነ ሃላፊ አስገድደህ እንዲፈጸምልህ የምትፈልገውን ጉዳይ ማስፈጸም ትችላለህ ሲሉ ሙሉ መብት ሰጥተውሃል።

ጠ/ሚ/ሩ አቶ ሃይለማሪያም ደሳለኝ ይህንን የመሰለ ድንቅ ስልጣን የሰጡህ በሚከተለው ምክንያትና መንገድ አገላለጽ ነው። የአቶ ሃይለማርያም ንግግር "ያለብንን የመልካም አስተዳደር ችግር ለመፍታት እኛ ብዙ ብንጥርም ህዝቡም በራሱ ማድረግ ያለበትን እንዲያውቅ እንፈልጋለን፡፣ አንድ ወዳጄ በአዲስ አበባ መስተዳድር ቢሮ ሲመላለስ የፈጸመውን ለአብነት ልንገራችሁ። ይህ ወዳጄ ጉዳይኑ ለማስፈጸም ሲሄድ ዛሬ አናስተናግድህም ይባላል፡፣ እሱም ይህ መብቴ ነው፣ አገልግሎት ማግኘት መብቴ ነው እና ጉዳዬን ዛሬውኑ ፈጽሙልኝ ቢላቸው የለም ፋይልህ ጠፍቷል ይሉታል። በዚህ ግዜ ከተቀመጠበት ወንበር ዘሎ በመነሳትና ፋይል መቀመጫ ሰብሮ በመክፈት ፋይሉን አውጥቶ ይህ የእኔ ፋይል አይደለም ጠፋ የምትሉት በማለት በሃይልና በጉልበት ጉዳዩን አስፈጽሞ መመለሱን አጫውቶኛል።
እናንተም ዝም ብላችሁ እሺ አትበሉ። በሃይል አስገድዱ።በተለይም ብትደራጁ ደግሞ ይበልጥ ማስገደድ ትችላላችሁ" ሲሉ በግልጽ ገልጸውልሃል።

ይህ የጠ/ምኒስትራችን ለመልካም አስተዳደር እጦት መፍትሄነት የተሰጠ መልስና ንግግር ነው። እናም በአመጽሕ ግፋበት፣ ተደራጅተህ እያስገደድክ ጉዳይህን እና መብትህን አስከብር ተብለሃል። [እኔ አላልኩም እሳቸው ናቸው፡ እኔ ይህን ካልኩኝ ዓመታት ነጉደዋል]

አስጨናቂው ህዝባዊው ዓመጽ ኢህአዴግን እንዲህ አድርጎ በማዝረክረክ እያናዘዘ ነው።

ጠ/ሚ/ሩ ሀገራዊውን የህዝብ ዓመጽና የሀይልም እርምጃን በተዘዋዋሪ መልኩ እየደገፉ ብቻ ሳይሆን መሆን ያለበትና እንዲሆንም እየፈቀዱ እንዳሉ አስተውለውት ይሆንን? ማስተስተዋል የሚችሉ ብጹዓኖች ናቸው። አስጨናቂው የህዝብ አመጽ የሰውዬን አስተውሎት ከመንሳቱም ባሻገር እንደ የሀገር መሪነታቸው እንካን የሀይል እርምጃ ምን ያህል ውድመትና ቀውስ እንደፈጠረ እያዩ ተመሳሳይ የሀይል እርምጃን ለመልካም አስተዳደራዊ ችግሮችን መፍቻነት ተምሳሌት አቅርበው ሲያበረታቱ ምን ልንል እንችላለን ሀገራችንን ማስተዋልን በተነጠቁ መሪዎች እንታደግ ከማለት በስተቀር።

የህወሃትና የትግራይ የበላይነት የለም ለማለት ሶስቱ ማለትም አቶ ሃይለማሪያም፣ ዶ/ር ደብረጺዮን እና አቶ ደመቀ ያልባጠጡት ቋጢኝ ያልፈነቀሉት አለት ባይኖሩም በሚደንቅ ሁኔታ ሶስቱም እየተቀባበሉ ማሳረጊያና መደምደሚያ ያደረጉት የህወሃትና የትግራይ የበላይነትን ያስነገሰው ጭራቁ ጥገኛ እንጂ ሁለቱም ሃይሎች የበላይ አይደሉም የሚል ነበር።

ስለዚህ በኢትዮጵያ ውስጥ የህወሃት የበላይነት ሳይሆን የጭራቁ ጥገኛ የበላይነት ነው ያለው ተብሎ ታውጃል።

እኔ የተጋራሁትና የማምንበትን አቶ ለማ መገርሳ "በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የአንድ ብሔር የበላይነት ሳይሆን የገዢዎች የበላይነት ብቻ ነው ያለው" የሚለው ድንቅ አቋም ነው።

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የአንድ ብሔር ትግራይ የበላይነት አለ የሚሉ ወገኖች በርካታ ናቸው። የሚያቀርባቸውም መሬት የማይጣሉ ጭብጦች እጅግ በርካታ ናቸው። ሆኖም መከራከሪያ ነጥቦቹ እና ጭብጦቹ የቱንም ያህል ተጨባጭ እና እውነታነት ያለው ቢሆንም የመጨረሻ የቀስት አቅጥጫው የሚያመራው የህወሃትን የበላይነትን የሚያሳይ እንጂ እንደ ህዝብ የትግራይ ህዝብ በተቀረው ወገኑ ላይ የበላይ ልሁን ብሎ ያደረገውን አይደለምና የአቶ ለማ መገርሳን በሀገራችን ታሪክ የነበረውና ዛሬም ያለው የአንድ ብሄር የበላይነት ሳይሆን የገዢ ሃይሎች የበላይነት ነው የሚለው አቋም ነው።

አቶ ለማ መገርሳ በማያሻማ መልኩ የህወሃት የበላይነትን የተጠቀሰውን ጭራቁን ጥገኛ ስም ሳያነሱ አስቀምጠውታል።

በነገራችን ላይ እነዚህ ጋዜጠኞች ከየት የመጡ ናቸው የትግራይና የህወሃት የበላይነት አለ እያሉ ጥያቄ ማቅረብ የቻሉት? ጋዜጠኞቹ ከዚህ በፊት ከሚያቀርባቸው ቆርፋዳ ጥያቄዎች ወጣ በማለት ብዙ እይታን የሰጡ ወቅታዊ ጥያቄዎችን ማቅረብ የመቻላቸው አበረታች ተግባር ሆኖ አይቼዋለሁ።

"ዴሞክራሲ የህልውና ጉዳይ ነው" የሚለውን እና ከመካከላቸው ሆኖ የተለየ እይታና አቋም ያንጸባረቀውን አቶ ለማ መገርሳን ከሶስቱ በቀቀን መሳይ የገደል ማሚቶዎች እኩል ላስተናገድው አልተቻለኝም።

"ታፍኖ የታናጠ ሁሉ ይፈነዳል" የሚለን አቶ ለማ "ኢትዮጵያዊነት እንደገበያ ሲያሻህ የምትበትነውና የምትሰበስበው ሳይሆን እጅግ ጥንታዊነት ያለው ታላቅ ረቂቅ ነው" በማለት በሶስቱ የህሳብ ድኩማኖች ፊት የሀገሪቷን ወቅታዊ ችግር ከሶስቱ በተለየ

ሁኔታን እውነታውን እያፍረጠረጠ ያቀረበልንን በማከሰኞው መጣጥፌ "የአቶ ለማ  መገርሳ ተመኩሮ" በሚል ርእስ ስር አጠቃላይ ቅኝቴን አቀርብላችሃለሁ።

"ጨቋኛ የአማራ ህዝብ የትግራይ ሕዝብ ጠላት ነች "በማለት በ1968ማንፌስቶው ላይ በግልጽ በማስፈርና የአማራን ህዝብ ከአቻው የትግራይ ህዝብ፣የኦሮሞ ህዝብና ከተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ነጥሎ ለማቃቃር የበላይ የሆነብህ ህዝብ ነው የሚለው የህወሃት ድርጅት ሊ/ር ዶ/ር ደብረጺዮን ባሉበት "በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የአንድ ብሔር የበላይነት ሳይሆን የገዢዎች የበላይነት ነው ትናንትም ሆነ ዛሬ ያለው " ያለን መሪ ዓላማ፣ራእይና አካሄዱን የሚቃኝ መጣጥፍ ለብቻው ማዘጋጀት ተግባሩ ያስገድዳል።

የአቶ ለማ  መገርሳ "የአንድ  ብሔር የበላይነት በታሪካችን ኖሮ አያውቅም " አባባልና አቋም ለዛሬው የትግራይ ህዝብ ብቻ የሚያገለግል ሳይሆን ትናንትን መሰረት አድርገው ሌላኛውን ብሔር የሚከሱና የሚያብጠለጥሉትንም ዝም የሚያሰኝ ሀገራዊ አቋም እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

በድጋሚ መልካም የገና በዓል ይሁንላችሁ-ቸር እንሰንብት።

--=------=---

አስተያየታችሁን እና ጥያቄያችሁን በኢትዮሚዲያ ኢ-ሜይል ወይም በግሌ teklu7@gmail.com  ብትጽፉልኝ እመልሳለሁ፡

Ethiomedia.com
January 7, 2018